# ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ኣክትሟል ወይ?

ገላውዴዎስ ኣርኣያ

## Have The Ethiopian Saints Reached a Vanishing Point?

Ghelawdewos Araia

This essay in Amharic attempts to address and critically examine the current situation in Ethiopia and makes an overview analysis of the complex political scenario, but more importantly it is an appeal to fellow Ethiopians, especially to those who are willing to make a sacrifice with determination and play a pivotal role in the positive transformation of their country. The leitmotif or running theme in this essay is 'unity and commonality of the Ethiopian people' and what Ethiopian progressive forces could do to make this objective a reality.

ኢትዮጵያ በሰው ልጅ ጥንታዊ ስልጣኔ ማእከላዊና ልዩ ቦታ ለመያዝዋ በተለያዩ ግዝያትና በልዩ ልዩ ጽሑፎቼ በማያሻማ መንገድ ኣቅርቤዋለሁ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨዋነትና ሃብታም ባህል፣ ጀግንነትና ባለታሪክነት በተደጋጋሚ በመጥቀስና በመተንተን ብያንስ ብያንስ በተለያዩ መድረኮችና የዜና ኣውታሮች ለሕዝብ ውይይት ኣቅርብያለሁ። የምያሳዝነው ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኣየር በጠባብ ኣመለካከትና በጎጥ ስሜቶች ስለተበከለ ዓብይ ጥያቄዎች እንደ ያገር ልዑላዊነት በሚነሱበት ግዜ ብዙ ኢትየጵያውያን (የተማርን ነን የሚሉም ጭምር) ከመጤፍም ኣይቆጥሩትም፣ በኣንጻሩ ጥቃቅንና ዝባዝንኬ የቡና ቤት "ፖለቲካ"፣ ግለሰቦችን መዝለፍ፣ ኣንድ ብሔርን ማጥላላትና ማንኳሰስ እንደ ስልትና ሞድ (fashion) በመጠቀም ለኢትዮጵያ ደሕንነት ለሚደረጉ ትግሎች ትልቅ እንቅፋት ሆነዋል። ከዚህ ጨምላቃ የፖለቲካ ክስተት በመነሳት ነው ደግሞ ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ኣክትሟል ወይ ብየ የምጠይቀው ያለሁት።

መቾም ለወደፊቱ፡ ተጨባጭ ያገራችን ሁኔታ ከፈቀደና የዓለምኣቀፍ የፖለቲካ ሃውም የሚስማማ ከመሰለ፡ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች የጎጥ ፖለቲካና ትምክህተኝነትን በመበጠስ ያገራቸውን ተሃድሶና ትንሳኤ እንደምያረጋግጡ እሙን ነው።

ሰሞኑን ብዙ የኢትዮጵያ ምእመናን ጾመ-ልጓሙ ይፈታላቸዋል፣ በዘልማድ ለብዙ ምእተ-ዓመቶች ስያደርጉት የቆየ 'ክርስቶስ ትንሳኤ ሙታን፣ ኣሰሮ ለሰይጣን ኣግኣዞ ለኣዳም' ብለውም መንፈሳቸውን ልያሳድሱ ነው። ልክ ክርስቶስ ኣዳምን ነጻ (ኣግእዞ) እንዳወጣው ሁሉ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆችም ሃገራቸውና ሕብረተሰባቸውን ነጻ ለማውጣት (ከጭቆና፡ ድህነት፡ ቸነፈር፡ ድንቁርና ወዘተ) ታሪካዊ ሓለፊነት ይሸከማሉ። በነገራችን ላይ፡ ክርስቶስ አዳምን ነጻ ያወጣው (ያግኣዘው) በደምና በመስዋእትነት እንጂ በትርኪ ምርኪና ኣታላይ የሓሰት

ፕሮፓጋንዳ ኣይደለም። አሁን ብዙ ኢትዮጵያውያን በቡና ቤት ፖለቲካ ስለተዘፈቁና መሪሕ የሚባሉ ድርጅቶችና ፓርቲዎች ደግሞ በኣርኣያነት ቀደምት ተግባሮች ማከናወን ስላልቻሉ የኢትዮጵያችን ጉዳይ ገና ነው የምያሰኝ ሆኗል።

ነገሩ ገና ነው ማለት ግን እጃችን ኣጣምረንና ተኮፍሰን ዝም ብለን እንለፈው ማለታችን ኣይደለም። በእርግጥ ለሁሉም ግዜ ኣለው የሚለውን የኣበው ኣባባል ከሞላ ጎደል እውነትነትና ርቱዕነትን የምያንጸባርቅ ነው። ሆኖም ግን ግዜም ሆነ ታሪካዊ ሂደቶች በኛ በሰው ልጆች ኃይል ነው ፈርና መልክ የሚይዙት፣ ደነዝ ስልቦች ኣይደለንምና! ስለሆነም ኣንዳንዶቻችን በመናግርና በመጻፍ፣ ገሚሶቻችን በቀጥታ ያለውን ስርዓት (ፖለቲካዊና ሕብረተሰባዊ) በመጋፈጥና በመታገል፣ ሌሎቻችን ደግሞ ሁለቱንም የትግል ስልቶች በማጣመር ሕብረተሰባዊ ለውጥ ለማምጣት እንታገላለን። የትግሉ ጎዳና ታድያ፡ ሁላችን እንደምናውቀው፣ ካለፈውም ሰላሳ ዓመታት ተሞክሯችን በቅጡ እንደምንገነዘበው ሁሉ፡ ለስላሳና የተስተካከለ ሊሆን ኣይችልም።

የትግሉ ጎዳና መስተካከል/ኣለመስተካከል ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ውስብስብነት ምክንያት ምንግዜም ግብን የመምታት ሁኔታና ውጤቶችን በቀላሉ መተንበይ የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፣ ኣንጻራዊ በሆነ መልክ ግን ሁኔታዎችን መገንዘብ ስለምንችል ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ካላከተመ በስተቀረ ኣገራችንን ለማንሳት የሚሳነን ነገር የለም። ኣገራችንን ለማንሳት ግን ብያንስ ብያነስ የሚከተሉትን መርሆዎች፡ ጽንሰ-ሓሳቦችና መንደርደርያ ነጥቦችን መከተል ይኖርብናል፦

- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጎሳ ፖለቲካና በጠባብ ብሔርተኝነት መነከር የለበትም። ነገር ግን የብሔር ስሜት፡ ዮጎጥ ፖለቲካ፡ የክልል ክንውኖች እንደ ሓጥያት መቆጠር የለባቸውም። እንድያውም የብሔሮች የራስ ገዝ መስተዳድር፡ ባህላቸውና ቋንቋቸው የሚያዳቡርበት መንገድ የምናበረታታው እንጂ የምንቃወመው ነገር መሆን የለበትም፣ ግን እንዲህ ዓይነቱ የክልል ፖለቲካ ከኣገር-ኣቀፍ ጥቅም ጋር የሚቃረን ደግሞ መሆን የለበትም። ባጭሩ፡ የክልሉ ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ኣገር-ኣቀፍ ጥቅም ግን ምንግዜም ልዑላዊነት እንዲኖረው ማድረግ ያሻል።
- ብሔር-ነክ ዘለፋና እርግማን ኣለማካሄድ። ለምሳሌ ‘ትግሬዎች (ትግራዎት) እንዲህ ናቸው’ ፣ ‘ኣማራ እንዲህ ናቸው’፣ በተጨማሪ የኣንድን ብሔር ተወላጆች በኣገር-ኣቀፍ (ኢትዮጵያውነት) ማንነታቸው እንጂ በብሔር ስማቸው መገለጽ ወይም መጠራት የለባቸውም፣ ለምሳሌ ‘እነዚህ ጉራጌዎች፡ ፡ ኣደሬዎች፡ ሲዳማዎች’ ናቸው። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር ቢኖር ለጥናትና ምርምር፡ በተለይም ለስነ-ሰው ና ለኅብረ-ትምህርት ጥናት ካልሆነ በስተቀረ የኣንድን ብሔር ግለሰቦች ወይም ስብስብ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እየታወቀ በጎሳ/ብሔረሰብ ወይም ብሔር ስም የሚጠሩበት ምክንያት ኣይታየኝም። በኢትዮጵያውነታቸው ከተጠሩና ከተገለጹ ኣንድነትና ወንድማማችነትን ነው የሚጐለምሰው፣ በጎሳ ስም ከተጠሩ ግን ኣዝማምያውና ዝንባሌው መለያየትና መገነጣጠል ነው የሚሆነው።

ፍርክስክሳችን ግን የሚወጣ አይመስለኝም፣ ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ካለከተማ በስተቀረ።

- ከፖለቲካው ስርዓት ባሻገር አንድን ብሔር በደፈናው ያለማውገዝ። ከዚህ ቀደም በሌላ ጽሑፌ እንዳቀረብኩት ሁሉ ማንኛውም ሰው ገና ለገና የዚሁ ብሔር አባል ልሁን ብሎ አይወለድም፣ እንዲህ ያለ ክስተት ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም፣ ለወደፊትም አይኖርም። ስለሆነም አንዳንዶቻችን የትግራይ ተወላጆች ነን፣ አንዳንዶቻችን ደግሞ አማራ፡ ኦሮሞ፡ አኝዋክ፡ አፋር ወዘተ ነን። ሌሎቻችን ደግሞ ወይ የሁለት ወይም ደግሞ የሶስት ብሔር ቅይጥ ልንሆን እንችላለን። ባሁኑ ግዜ ደግሞ ቅይጥነት ማለፍያ ነው የምያሰኝ ሳይሆን አይቀርም፣ ምክንያቱም ለአንድነታችን አመቺ ሁኔታ ይፈጥርልናል። የሆኖ ሆኖ ግን ይኸንን ነጥብ ያነሳሁበት ምክንያት አንድን ብሔር ወይም የአንድን ብሔር ሰዎች በደፈና ከማውገዝ ይልቅ ያለውን የፖለቲካ መዋቅርና የመደብ አሰላለፍ በጥልቀት መመርመር አስፈላጊ እንደሆነ ለማስታወስ ያህል ነው። ለምሳሌ፡ በአጼ ኃይለስላሴ ግዜ የአማራ ብሔር የሚወገዝበት ግዜ ነበር፣ በተሳሳተ መንገድም አማሮች በሙሉ የመደብ ተጠቃሚዎች እንደነበሩ ይቀርብ ነበር። በእርግጥ ተጠቃሚዎችና ነፍጠኞች ነበሩ፣ ግን በድህነትና በቸነፈር የሚሰቃዩ፣ የዕለት ዳቦ የማያገኙ፣ ደህናም ከተባሉ በደሳሳ ጎጆ የሚኖሩ አማሮች እንደነበሩና እንዳሉ የምናውቀው ሓቅ ነው። ከፍ ብየ እንደጠቀስኩትም የዚሁ ብሔር ተወላጆች ሆን ብለው ማንነታቸውን የለጠፉ ሳይሆን እንዳጋጣሚ የሆነ ነገር ነው። በተጨማሪ የዚሁ ብሔር ተወላጆች፡ እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን፡ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ታግሏል።
- ለአማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ያደረግነውን ገለጻ ለሌሎች ብሔሮች ማድረግ ሓለፊነት አለብን። በዚሁ መጠነኛ ሓተታና አቃቂር ግን የሁሉም ብሔሮች ማስቀመጥ ስለማይቻል ካሁኑ ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር ብቻ የሚሄድ ልጥቀስ፦ አጋጣሚ ሆኖ አሁን ኢትዮጵያን የሚገዛው ያለ ፓርቲ ኢህአዲግ ነው፣ ከዚሁም ፓርቲ ዋናው የፖለቲካ ድርጅት ሕወሓት ነው፣ ሕወሓት የትግራይ ተወላጆች ፓርቲ ለመሆኑ አንድም ሁለትም የለውም። ድርጅቱ በትረ-ስልጣኑን በመጨበጡ ግን የትግራይ ሕዝብ በጠቅላላ ስልጣን ላይ ቁጢጥ ብለዋል ማለት አይደለም፣ ምልአተ ሕዝቡዩም ተጠቃሚ ነው ማለት አይደለም። እላይ እንደተመለከትነው አሁንም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ ከቸነፈርና ድህነት አልተላቀቀም፣ በደሳሳ ቤትም የሚኖር ሕዝብ በርካታ ነው። የዚሁ ብሔር ተወላጆች፡ እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ ነጻነትና አንድነት ተዋግቷል፣ ከፍተኛ መስዋእትነትም ከፍለዋል፣ የገድለ-ጻድቃናት ተልእኮ አሟልቷል።
- አሁንስ የገድለ-ጻድቃናት ተግባሮች ማድረግ እንችላለን ወይ? ማድረግ የምንችል ከሆነ እርስ በራሳችን መዋደድ፣ መከባበር፣ መተዛዘን፣ ከዛም ለጥቆ የሁላችን መለዮ በሆነው (የጋራ ማንነታችን) ከ 'ኢትዮጵያውነት' ጋር በማዛመድ የተባባረ ክንድ መፍጠር ይኖርብናል። በጋራ ማንነታችን የምንተቃቀፍና የምንከባበር ከሆነ ደግሞ ወዳጆቻችን ያከብሩናል፣ ጠላቶቻችን ደግሞ ይርበደበዳሉ። በትርኪ ምርኪ ፖለቲካ ካተኮርንና እርስ በራሳችን ከተበላላን ግን ወዳጆቻችን ያዝናሉ፣ ጠላቶቻችን ይፈነጥዛሉ።

ይኸንን መፍቀድ የለብንም፣ ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ካላከተመ በስተቀረ።

- ሰው-በላ ፖለቲካ ለማሰውገድ (ለዘለቄታው ማለቴ ነው) ከፈለግን ደግሞ ንቃተ-ኅሊና፡ ጽናትና እምነት ነው የምያስፈልጉን። ንቃተ-ኅሊናችን በጣም ከዳበረ ኣጉል፡ ስንኩልና ጠባብ የፖለቲካ ኣመለካከትን በጥሰን ማለፍ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ስርዓቱን ባህርይና ይዘት በጥልቀት መገንዘብ ስለምንችል ወደ እርግማንና ዘረኛ የመርዝ ፖለቲካ ኣናዘነብልም። እምነት (ቆራጥነት) ካለንና ጥናቱን (ጽናቱን) ከሰጠን ደግሞ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፕሮግራሞችን ከመተግበር የምያግደን ኃይል ኣይኖርም። እንደገና ወደ 'ንቃተ-ኅሊና' እንመለስና በጣም የነቃና የተደራጀ የሕብረተሰባችን ክፍል ሰፋ ያለ የፖለቲካ ኣጀንዳ የምያራምድ ከሆነ የጎጥ ዝንባሌዎችና ስሜቶች የኢትዮጵያ ጥንታዊና መሰረታዊ ቃጫዎችን ሲሸረሽሩና ሲበጣጥሱ ዝም ብሎ ማየት ኣይችልም። ባጠቃላይ ምልኣተ ሕዝቡ በዓብይ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ እንድያተኵር ይረዳል፡ ያስተምራል፡ ይመራል።
- ሰፊ የፖለቲካ ኣመለካከት ካለን ከቂም-በቀል ፖለቲካ ነጻ እንሆናል፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከኢትዮጵያ ኣብራክ መፈጠሩን እናምናለን፣ እናከብራለን፣ ቅራኔዎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እንሞክራለን፣ የፖለቲካ ችግሮችን በዘዴና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለመወጣት እንጥራለን፣ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ መብት በሕግ ፊት እንዲተገበር እንጠይቃለን፣ የዴሞክራሲ ግንባታ የጋራ ሓለፊነት መሆኑን ተገንዝበን ጭቃ ማብኳቱና ኣለቱን መፍለጡ የጋርዮሽ ግብረ-ኃይል መሆኑን ኣጥብቀን እንረዳለን፣ ስልጣን ሓላፊናትና ተጠያቂነት እንጂ የኣንባገነንነት መናኸርያ እንዳልሆነ እንገነዝባለን። እነዚህን ሁሉ በግብር ማሟላት ከበቃን ደግሞ ወደ ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ተጠግተናል ብንል የተጋነነ ኣይመስለኝም፣ ምናልባት ግን የሚቀረን ኣንድ ተጫማሪ መርሆ ሊኖር ይችላል፡- ይቅርታ ማድረግና ኣገር-ኣቀፍ ዕርቅን ማከናውን።
- ይቅርታ ማድረግ ከባህላችንና ከኃይማኖታችን የመነጨ ጨዋ ወግ ነው፣ ለጠላትም ሳይቀር ምሕረት ይደረግለት ዘንድ ወጉ ይፈቅዳል። ይቅርታን ተከትሎ ምሕረት ከታወጀ ደግሞ ኣገር-ኣቀፍ ዕርቅ ለማካሄድ በፍጹም ኣያዳግትም። ለምሳሌ በገዢው ፓርቲ በኢህኣዲግ ዙርያ ያሉ ባለስልጣናትና በተቃዋሚ (ቅንጅት፡ ኅብረት ወዘተ) ኣካባቢ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ከኢትዮጵያ ኣብራክ የመነጩ ስለሆነ እርስ በራሳቸው ይቅርታ ተቀያይረው ለኣገራዊ ዕርቅና ደርድር መቅረብ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን የፖለቲካ ስልጣንና ኃይል በኢህኣዲግ ዙርያ ስለተከማቸ የምሕረቱና የዕርቁ ጉዳይ ማመንጨት ያለበት ኢህኣዲግ ነው። ግብረ-ኃይሉንም ፈር በማስያዝና በማስጨበጥ በእስር ቤት የተወረወሩትን ግለሰቦች ነጻ ማውጣት ኣለበት። የውጭ ዲፕሎማቶችና ፖለቲከኞች ሓሳብ ስላቀረቡና ይፈቱ ስላሉ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስት በገዛ ራሱ የወሰናቸውን የፖለቲካ እርምጃዎችን ነው ቀዳሚነት መስጠት ያለበት። በሌላ ጽሑፌ እንደገለጽኩት ሁሉ ከመጀመርያውኑም የቅንጅት ሰዎች መታሰር ኣልነበረባቸውም። እንድያውም ኢህኣዲጎች ቅንጅቶችን ከማሰር ይልቅ የኢትዮጵያን ወጣት በይፋ (ቀይ ሽብር) የጨፈጨፉትን የመንግስቱ ኃይለማርያምና የባልደረቦቹ ቡድን ለፍርድ ማቅረብ ነበረበት። ከሕግ በላይ (ሕግ-የለሽ ስርዓት) ሆኖ ሕዝብን

የጨፈጨፈ ነው ወንጀለኛ ወይስ በሕጋዊ መንገድ ለፖለቲካ ውድድርና ምርጫ የተሰለፈ ኣካል? ኣሁን ግን ላለፈ ቤት ክረምት ኣይሰራለትምና፡ ቅንጅቶቹ ተፈተው ዕርቅ ይደረግ። ኢህአድግ ቅንጅቶችን ነጻ ካወጣ ራሱን ነው ነጻ የምያወጣው፣ ብያንስ ብያንስ ኣገራችንን ከጥፋት እናድናታለን፣ ሁላችንም በጋራ ወደ ገድለ-ጻድቃናት እንጠጋለን።

- እንግዲህ ሰፋ ያለ የፖለቲካ ኣጀንዳ በሚመለከት ከተነጋገርን ኣይቀር ሌላ ሰላም-ነክ ጉዳይ ላክልበትና የኤርትራና ኢትዮጵያ ውስብስብ ፖለቲካ ላስምርበት። እርስ በራሳችን ለምናደርገው ዕርቅና ድርድር ሰፋ ባለ መልኩ ከተጠቀምንበት በኛና በኤርትራ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ዘለቄታ ያለው ዕርቅና ሰላም መደረግ ኣለበት የሚል እምነት ኣለኝ። በእርግጥ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና ልዑላዊነትን የሚጻረሩ እርምጃዎች ከተወሰዱ ኣሁንም ቢሆን በጸና እምነቴ እታገላቸዋለሁ። ሆኖም ግን ያለፈው ኣልፈዋልና ከእንግዲህ ወዲህ ሁለቱ ሕዝቦች ጎን ለጎን በሰላም ለመኖር የሚቻልበት ስትራተጂ መቀየስ ይኖርብናል። የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በብዙ ረገድ የተቆራኘ ሕዝብ ነው፣ ሁለቱ ሕዝቦች በቋንቋ፡ በኃይማኖት፡ በባህልና በታሪክ የተሳሰሩ ናቸው። እንኳንስ በጦርነት ሊፋላለጉና ኣነስተኛ ጠብና ኣምባጓሮ እንኳን በመኻላቸው መጫር ኣልነበረበትም። ታድያ በሁለቱ ሕዝቦች መሃከል የመቀራረብ መንፈስ እንዲኖርና የሰላም ድልድይ እንዲገነባ ከተፈለገ የምሉ ውህደት ስትራተጂ እንኳን ባንቀይስ፡ ብያንስ ብያንስ የኮንፈደረሽን ወይም ፈደረሽን መዋቅሮች እንዲዘረጉ ማድረግ ግን ተገቢ ይመስለኛል። ይህ ኣጀንዳ በግብር ከተተረጐመ ደግሞ…ኣቤት ኣቤት ወደ ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ እጅግ በጣም ተጠግተናል ማለት ነው።

ኣሁን ወደ ርእሰ-ነገሩ ፍሬ-ነገር ልመለስና ይኸንን ለመንደርደርያ ያህል ያቀረብኩትን የውይይት ነጥብ ባቀረብኩት ጥያቄ ላሳርገው። ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ኣክትሟል ወይ? እኔ ሁሉ ግዜ ብሩህ ተስፋ ነው የሚታየኝ፣ በቀላሉም ተስፋ ኣልቆርጥም። ስለሆነም የኢትዮጵያ እውነተኛ ልጆች ተዳክመዋል እንጂ ኣልጠፉም፣ ተኝተዋል እንጂ ኣልሞቱም፣ እንደ ቀን ጣይ የለም ሆኖባቸው እንጂ ኣልተበገሩም። ይኸንን ርትዓዊ ኣመለካከት ከተቀበልን እንግዴህ ገድለ-ጻድቃናት ዘኢትዮጵያ ኣላከተመም! እንዴትስ ብሎ ያክትም? የብዙ ሺ ዘመን ስልጣኔ፣ ጠንካራ እምነትና ልምድ፣ ግዙፍ የፖለቲካና የስነ-መንግስት ባህል፣ በራስ የመተማመን፡ ብሔራዊ ኩራትና ኣገር-ወዳድነትን ያጣመረ መሰረታዊ ውስጠ-ቅርጽ በቀላሉ ኣይጠፉም። ግን ለዚሁ ሲወርድ ሲዋረድ ሲተላለፍ የቆየ ባህል ለመጠበቅና ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ የፖለቲካ ብልሃትና ጠቢብነትን ይጠይቃል። እኛ የበለጸገ ምጣኔሃብታዊና የመጠቀ ዘበናይ ተክኖሎጂ የለንም እንጂ በምድረ ኢትዮጵያ ብልሃተኞችና ጠቢባውያን እንደኣሸን ናቸው! ታድያ ምን ዋጋ ኣለው ለመብዛታቸው፣ ኣብረው እስካልሰሩ ድረስ የምንፈልገውን ግብ ልንመታ ኣንችልም። ብልሃቱም ዕርቁም የሚፈለገው ለዚሁ ነው። የጻድቃናት ገድልና ተግባርም ከዚሁ የተለየ ሊሆን ኣይችልም።

Copyright © IDEA, Inc. 2006